# ማን ያውራ የነበረ
# ለኢትዮ ፓትሪዮትስ ድረ ገጽ አንባቢያን

ከአቶ ሰውየው በሀገሩ (ዘብሔረ ኢትዮጵያ!) - ከሰሜን አሜሪካ

መናኛ የታሪክ ላጲሶች በደም በመሥዋዕትነት የተጻፉ
የትግል ታሪኮችን ሊያጠፉት አይችሉም!

በቅርቡ አቶ ጌታቸው ረዳ (ዘብሔረ አክሱም) የማያውቀውን በደምና በመስዋዕትነት የተጻፈን የኢሕአፓንና የዚያን ጀግና ትውልድ ታሪክ ለማጥላላት ሲሞካክር ለሰጠሁት መልስ (http://assimba.org/Articles/Open_Letter_To_Ato_Getachew_Reda.pdf) በተደጋጋሚ የውሸት ቆርጦ ቀጥል አፈ-ታሪክ ቢዚህ ድረ-ገጽ ማዥጎድጎድ የቀጠለ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። ዛሬ ወያኔ በሕዝብ ጥላቻና ትግል ወደትቢያ ሊወድቅ በሚንገዳገድበት ወቅት ጌታቸው ረዳና መሰሎቹ የለም ጠፍቷል በሚሉት ኢሕአፓና በዚያ ትውልድ ታሪክ ላይ ለምን መዝመት አስፈለጋቸው የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ እነሆ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በየጊዜው ኢሕአፓን ለሚከሱ ሁሉ መልስ የሚሰጡ **"ማን ያውራ የነበረ"** በሚል ርዕስ በተከታታይ እስከ 15 ቁጥር ከቀረቡት መካከል ከሚቀጥለው ገጽ ጀምሮ ቁጥር 13፣ ቁጥር 14፣ እና ቁጥር 15ን አንብባችሁ በሌላው በኩል ያለውን እንድትመረምሩ በማክበር እጠይቃለሁ። ምናልባትም የሻለቃ ፍስሐ ደስታን መጽሐፍ ባዳነቀበት አዕምሮው እነዚህን መጣጥፎች አንብቦ አቶ ጌታቸውም የዚያን ትውልድ ዕውነተኛ ታሪክ ያጤነዋል ብዬ እገምታለሁ።

አቶ ጌታቸው ረዳ "መልስ ለአሲምባ "የኢትዮጵያ ሕዝብ አራዊቶች ፓርቲ" ድረገጽ ጌታቸው ረዳ(ኢትዮ ሰማይ አዘጋጅ)" በሚል ርዕስ ላቀረበው ጽሑፍ እንደ አሲምባ ድረ-ገጽ አዘጋጅነቴ ብዙ ማለት ብችልም በራሱ ጽሑፍ የራሱን ማንነት ያጋለጠ ስለሆነ በአሁኑ ዙር እንኪያ ሰላምታ ልገጥመው አልፈልግምና ፍርዱን ለአንባቢያን እተወዋለሁ። በጽሁፉ መጨረሻ የማን ያውራ 15ቱንም ቁጥሮች ልታገኟቸው የምትችሉባቸውን ጥቆማዎችን አካትቻለሁ። ከዚህም ሌላ ዛሬ ያለንበትን የሀገራችንን ሁናቴ የሚዳስስ በቅርቡ የወጣውን የአሲምባ ድረ-ገጽ ርዕሰ አንቀጽ "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" በሚል ርዕስ የተጻፈውን እንድታነቡም እጋብዛለሁ።

በመጨረሻም የኢትዮ ፓትርዮት ድረ-ገጽ አዘጋጆች የሁሉንም ወገን አስተያየት በማቅረብ የሁሉም ወገን ድምጽ እንዲሰማ ማድረጋችሁን በግሌ አመሰግናለሁ።

አቶ ሰውየው በሀገሩ (ዘብሔረ ኢትዮጵያ) - ከሰሜን አሜሪካ

መናኛ የታሪክ ላጲሶች በደም በመሥዋዕትነት የተጻፉ
የትግል ታሪኮችን ሊያጠፉት አይችሉም!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

የሚዘምተው፡፡ አለምክንያት አይደለም ለመዋሸት የተገደዱት፡፡ ሌሎች ደግሞ ሀሰቱ ሀቅ እየመሳላቸው በመሳሳት ነው፡፡

ጥያቄ-- እሰቲ በምስረታው እንነሳና ኢሕአፓን የመሰረተው በእውነት ሻዕቢያ ወይም የኤርትራ ግንባሮች ነበሩ?

መልስ-- ይህ በተደጋጋሚ የተነገረ ውሸት ነው፡፡ ኢሕአፓን የመሰረቱት የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪዎችና አባሎች የነበሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ከተማሰሪ ማህበር ባሻገርና በላይ ትግሉ በፖለቲካ ድርጅት መልክ መካሄድ አለበት ብለው ያመኑና በልዩ ልዩ ቦታ የነበሩ እነዚህ ታጋዮች ተቀናጅተውና በተለይም በሀገር ቤት ከነበሩት ጋር ተያይዘው በ1964 ዓ.ም. ኢሕአፓን መሰረቱ፡፡ በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አባል የነበሩና ለኤርትራ ነፃነት መታገል ይሉ የነበሩት የኤርትራ ተወላጆች ወደ ሻዕቢያና ጀብሀ ሄደው ተቀላቅለው ነበር እንጂ ያን አቅዋም ይዘው በእንቅስቃሴው አልቀጠሉም፡፡በእንቅስቃሴው የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ውልደታቸው ከኤርትራ/ ስለነበር ብቻ ወደነ ጀብሀና ሻዕቢያ መለጠፉ ስህተት ነው፡፡ወያኔና ሻዕቢያ ስልጣን ሲይዙ የተሸበሩ ክፍሎች ተሰፋ እየቆረጡ ድሮም ቢሆን እነሱ ናቸው ሁሉን ያኬሄዱት የሚል እጅ የሰጠ የዝቅተኝነት ስሜት ያንፀባርቃሉ፡፡ ይህ ግን መሰረተ ቢስ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ራሳቸውን በቻሉ ምሁሮች የተመራ ለኢትዮጵያ የታገለ እንቅስቃሴ ነበር፡፡ ኢሕአፓም ሲመሰረት ጀምሮ ይዘቱ ህብረ ብሄራዊ ነበርና በውስጡ የነበሩት ከልዩ ልዩ ብሄረሰብ የተወለዱ ኢትዮጵያውያን ነበሩ/ናቸውም፡፡ ከኤርትራ ግንባሮች ጋር ኃሏ ያደረገው ግንኙነት ደግሞ ትግሉ ግድ የሚለው ነበር፡፡

ጥያቄ-- ግንኙነቱ እንዴትና ለምን ተመሰረተ ?

መልስ-- ኢሕአፓ የነበረውን ስርዓት በትጥቅ ትግል ማስወገድ የግድ ነው ብሎ ያመነ ድርጅት ነበር፡፡ ሰለዚህም የታጠቀ ኃይል በመጀመሪያ አሰልቋ/ኖ ሊያስገባ ያሰበው በባሌ በኩል ስለነበር በወቅቱ የጫካ ትገል ይመሩ ከነበሩት ከእና ዋቆ ጉቱ ጋር በሶመላሻያ በኩል ለመገናኘት ጥሯል፡፡ በዚያድ ባሬ መንግስት ሻጥር ይህ ጠረት ሳይሳከ ሲቀር ደግሞ በሱዳን በኩል ሌላ ሙከራ ተደርጎ ይህም አልተሳካም፡፡ በመጨረሻም በትግራይ በተለይም በአዲ ኢሮብ በኩል መጀመር የተባለው በግድ ከኤርትራ ግንባሮች ጋር ግንኙነትን የሚጠይቅ ነበር፡፡ በዚያ ለማለፍ፡፡ ኢሕአፓ በመጀመሪያ የነበረው ግንኙነት ከጀብሀ ጋር ነበር፡፡ ኋላ ደገሞ ሻዕቢያ ሲቋቋም ከእነሱም ጋር ተገናኝቷል፡፡ የኤርትራ ግንባሮች መሰራቸውን አስተካክለው በጋራ ለኢትዮጵያ እንዲታገሉ ይጥር ነበር፡፡ የሕዝብን መብት አውቃለሁ ቢልም ለግንባሮቹ ሙሉ ድጋፍን የሰጠበትና ለሕዝብ ይጠቅማሉ ያለበት ጊዜ የለም፡፡ ሻዕቢያ ኤርትራ ቅኝ ግዛት ናት በሉ ያለውንም ኢሕአፓ አልቀበል ስላለ ተሯሩጦ ወያኔን ምስረታ ሂደቱን ደግፎ በትግራይ የሚያገለግለውን ቡድን ቀድሞ ወደ ትግራይ አስገባ፡፡ በወቅቱ በሻዕቢያ ውስጥ ችግር ሲፈጠርም የተሻለ አቅዋም የነበራቸውንና መንክዓ የተባሉትን በምስጢር በመተባባር የተሻለ መስመር ይሰፍን ዘንድ ኢሕአፓ በአቅሙ ሞክሯል፡፡ ጀብሀም የፋሉል ችግር ሲነሳበት ተመሳሳይ እርምጃን ኢሕአፓ መውሰዱ ይታወቃል፡፡ በአጭሩ ኢሕአፓ ትግሉን ወደ ፊት ለማራመድ መወሰድ የነበረበትን ግንኙነት ቢያደርግም ዓለማውን ወይም መርሁን ወይም የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ አልሰጠም፡፡

ጥያቄ-- በቅርቡ በሀገር ቤት በየወሩ እየታመ በሚወጣ መፅሔተ ላይ አንድ የኢሕአፓ መስራች ነበርኩ ግን በኤርትራ ጥያቄ ተለይቼ መኢሶን ሆንኩ የሚል ግለሰብ ድርጅቱ ከግንባሮቹ ነበረው ስለሚለው  ግንኙነት የፃፈውን አነበናል፡፡ ሌሎች ደግሞ እነ ኢሕአፓ ወይም የተማሪው አንቅስቃሴ በግንባሮቹ ተዘውረው የመገንጠልን አማራጭ ደገፉ ይላሉ፡፡ አንድ በአውሮጳ ያለ በደርግ ዘመን የደርግ ደጋፊ የነበረ  ምሁር ደግሞ ሻዕቢያና የአሜሪካው ሲአይኤ ኢሕአፓን የመሰረቱት የመሩት እስከማለትም ደርሷል፡፡ ሀቁ የት ነው?

መልስ-- ኢሕአፓ በአረቦች፤በነሻዕቢያና በአሜሪካ የስለላ ድርጅት ተካሄደ ብሎ መለፈፉ ያዋጣኛል ብሎ የጀመረው ደርግ ነበር፡፡ ልጆቹና ሎሌዎቹ ቀጥለውበታል፡፡ የአረብ ፔቴሮዶላር ወይም የቤንዚን ገንዘብም የሰጠዋል ሲባል ነበር፡፡ ግራ ክንፉ ደርግ እንግዲህ ኢሕአፓን በአሜሪካና በአረብ አደሀሪዎች ቅጥረኝነት ሲከስ መሆኑ ነው፡፡ የደርግ ምሀሮች የነበሩና ሰነዱን ሲተረጉሙና ተራማጅ ነው ሲሉ የነበሩ ሳሬን ይህን ሀሰት ቢነዙ አይገርመንም፡፡ ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የታገለ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ድርጅት ነበር፡፡ መስራች ነበርኩ ወደ መኢሶን ገባሁ ባዩ ግለሰብ ዋሾ ቁጥር አንደ ነው፡፡ የመስራች ትርጉም እስካልተቀየረ ድረስ በኢሕአፓ መስራች ጉባዔ ተገኝቶ ወደ መኢሶን የገባ በህይወት ያለ ግለሰብ የለም፡፡ በሀዋስ የኢሕአፓ አባል ሆነው ወደ መኢሶን ላላ ከሄዱት ሶስት ግለሰቦች መሀል ሁለቱ በደረርግ ሲገደሉ አንዱ አሁንም በእርግጥ በህይወት አለ ፡፡ ዋናው ዓላማ ግን ኢሕአፓ ከግንባሮቹ ገጥሞ አጀንዳ አራመደ ወይም ደገፍ የሚለውን ለማናፈስ ነውና ይህ ደግሞ ሀሰት ነው፡፡ የሕዝብን ትግል መደገፍ ሌላ ግንባርን መደገፍ ሌላ የሚለውን አቅዋም ያኔም ኢሕአፓ የረሳ ወይም ቸል ያለ አልነበረም፡፡

ጥያቄ-- የመገንጠልን መብት ኢሕአፓ ያውቅ ነበር ግን?
መልስ-- በቅድሚያ ኢሕአፓ ከመፈጠሩ በፊት የብሄረሰብ ጥያቄዎችና አመፆች ነበሩ፡፡ የጀብሀ ትግል ሲጀምር ይህ ነው የሚባል የተማሪ አንቅስቃሴ በሀገራችን አልነበረም፡፡ የአነ ዋቆ ጉቱ የባሌ ትግል፤ የአጋዴነ አመፅ፤ የሜጫ ቱለማ  ትግል ወዘተ ሁሉም ኢሕፓን በዓመታት ይቀድማሉ፡፡ ስለዚህ ኢሕአፓ ወይ የተማሪው እንቅስቃሴ ያለነበረን ችግር ቆፍረው አውጥተው እባካችሁ ተነሱና ተገንጠሉ አላሉም፡፡ የእኩልነተና የመብት ችግር ነበረ ፡፡ እንገንጠል ያሉ ነበሩ፡፡ ሕዝብን በህብረት ለማታገልና የሀገርን አንድነት ለሙብቅ መን አቅዋመ መያዝ አለብን ለሚለው በእነ ኢሕአፓ የተሰጠው መልስ የራስን ዕድል በራስ አስከኸወሰን ድረስ የመለውን ማወቅ የሚል ነበር፡፡ ይህ ግሞ ያኔ እንቅስቃሴዎችን የሚመራ በነበረው ርዕዮተዓለም መሰረት የመገንጠልን መብት ማወቅ መገንጠልን ከመደገፍ በተለየ መልክ መቀበል የሚል ነበር፡፡ ስለዚህ መብት ቢያውቅም መገንጠል ደግሞ አይበጅም ሲል ኢሕአፓ ግልፅ አቅዋም ያዘ ፡፡ ለዚህም ነወ. ከመጀመሪያ ጀምሮ የኤርተርሮን ቅኝ ግዛትነት ያልተቀበለው፤ የወያኔን የግንጠላ ማኒፌስቶ የተቃወመው፡፡ ለመሆኑ ዛሬ ኢሕአፓን የሚያወግዙት ክፍሎች ያኔ ከጠባቦች ወይ ከጨቋኞች ይታገሉ ነበር? ሌላ የተሻለ አማራጭን አቅርበው ነበር? ደርግ በአስመራም ሲጨፈጭፍ አወገዙትና ከወንድም እህት የኤርትራ ሕዝብ ጎን ቆሙ ወይስ በለው ብለው ግፉን አጀቡ?ስለዚህም ኢሕአፓ እውን የግንባሮቹ ጭፍን ወዳጅና ደጋፊ ከነበረ ለምንስ ሊያጠፉት በየፊናቸው ተንቀሳቀሱ? የሀሰት ፕሮፓጋንዳው ከሀቁ ጋር የተጣለ ነው፡፡ ሀቁ የሚያሳየው ኢሕአፓ ኢትዮጵያዊ አቅዋሙን ይዞ መቀጠሉንና በዚህም የተነሳ በእነ ሻዕቢያም በባዕዳንም መጠቃቱን

ነው፡፡ኢሕአፓ ሀገር ብሎ ሲታገልና ለሕዝብ አንድነት ሲዋደቅ በነበረበት ጊዜ ዛሬ ሀገር ወዳድ በሉን ባዮች ግን ወይ ከጨቋኞች ጋር ገጥመው የሕዝብ አንድነትን ሚጎዱ ነበሩ ወይም ከጠባቦቹ ጋር ሸብ ረብ ሲሉ የነበሩ ናቸው፡፡ ወያኔ ለስልጣንን ሲበቃም ባልተናነሰ ጠባብነት ወይ ትምክህት ጎዳና የተጓዙት ዛሬ ተመልሰው ኢሕአፓን ሊከሱ የሞራል ብቃት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ እነ ወያኔ ኢሕአፓን አባይ ኢትዮጵያ ወይም የትልቋ ኢትዮጵያ ጠበቃ ብለው በእነሱ ቤት በክፉ ሲሰይሙት ይህ ራሱ የሚያሳየው የኢሕአፓ አቀዋም ምን እንደነበረ ነው፡፡ ኢሕአፓ ሀገርን የሚጎዳ አቅዋም ይዞ በነበረ ሀገርን ሊገነጥሉ በተነሱት ባልተወገዘም ባልተወጋም ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በሀገራችን የነበረውንና ያለውን የእኩልነት መጥፋት የሚክዱና በትምክህት የሚዋጡ ክፍሎች ደግሞ ኢሕአፓ የሕዝብ መብትና እኩልነት ይከበር ሲል ያማቸዋል፡፡ ስለዚህም ገንጣይ ብለው ሊከሱት ይፈልጋሉ፡፡ ህብረ ብሄራዊ ይዘቱ ይጎረብጣቸዋል፡፡ዛሬ ወያኔን ተቃዋሚ ነን ቢሉም ከወያኔያዊ ወይም ትምክህተኛ ክፉኝ ተከትበው የዳኑ አይደሉምና አቅዋማቸው ብልሹ ነው፡፡ የአባዬን ለእምዬ ባይ ናቸውናም ኢሕአፓ ላይ ይዘምታሉ፡፡ ጣብ የሆኑ ድርጅቶች ደግሞ ለምን የሕዝብን አንድነት ሰበከ ፀሚል ይዘምቱበታል፡፡ የግንጠላ አጀንዳቸውን ሰለማይደግፍ ነው፡፡ ኢሕአፓና የኦሮሞ ሕዝብ ትግል በሚለው ዕሁፍ ድርጅቱ በዚህ ላይ በሰፊው ተችቷል፡፡በአጠቃላይ በድርጅት ደረጃ ለትግሉ አሰፈለላጊ የሆኑ ግንኙነቶችን መመስረት ማለትና የሌሎችን አቅዋም ውጦ ማስተጋባት ወይም በጭፍን መደገፍ ማለት በጣም የተለያዩ ናቸው፡፡ ቢያንስ ለኢሕአፓ፡፡ ወያኔ፣ የደርግና የወያኔ የገደል ማሚቴዎች ይህ ባይገባቸው አይገርመንም፡፡

ይቀጥላል........

## በፍኖተ ዴሞክራሲ ሬድዮ
## ሚያዝያ 22/97 (አፕሪል 30/05( የተላሰፈ፥

## ማን ያውራ የነበረ (ቁ. 14)
## በጥያቄና መልስ --ክፍል ሁለት

*ጆሮ ያለው ይስማ ዓይን ያለው ይይ ስለተባለ፥ ሁሉም ሁሌም ባለው ይገለገላል ማለት ስላልሆነ፥ ደግመን ደጋግመን የነበረውን በማቅረብ የታሪክ በራዦችን ሴራ ለማክሸፍ ትግላችን ይቀጥላል። ስለዚህም ማን ያውራ የነበረ በጥያቄና መልስ መልክ ይቀርባል።*

*ጥያቄ-- ኢሕአፓ ለሥልጣን እንጂ ለሕዝብ አልታገለም/አይታገልም። አባሎቹ ከሀገር ይበልጥ ድርጅታቸውን ያስቀድማሉ። በቅርቡ አንድ ደራሲ የሆኑ አዛውንት በአንድ መፅሔት ሲተቹ ኢሕአፓ አናርኪስት ኒሂሊስት፤አጥፊ እንጂ ገንቢ አልነበረም ይላሉ። ለዚህ ምን ምላሽ ይሰጣል?*

*መልስ-፡ አዛውንቱ፥ ኢሕአፓ ጨቋኙን ሥርዓት መጣል-ማውድም ይፈልጋል ማለታቸው ከሆነ ልክ ናቸው። ግን የድርጅቱ ዓላማ ያለውን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የተሻለና ሌላ፤ በይዘቱና በዓይነቱም የተለየ ሕዝባዊ ሥርዓት ለመመስረት ነበር።ነውም። ፕሮግራም ያወጣነው ለምንና ለማን እንደምንታገል፤ ድልን ከተቀዳጀን ደግሞ ምን ዓይነት ሥርዓት ይመስረት ብለን እንደምናምን ለማሳየት ነው። ከዚያ ባሻገር ግን የሀገራችን ምሁሮች እንደ ኮለኔል መንግስቱ ጥራዝ ነጠቅ ሆነው የሆነ ያልሆነውን ቃል ባይወረውሩ ተገቢ ነው። አናርኪስት ወይም ሥርዓት አልበኝነት የፖለቲካ ርዕዮትና አቋም ነው። ኒሂሊዝም የሚባለውም እንዲሁ። ከኢሕአፓ አቋም ጋር አንድ አይደሉም። ኢሕአፓ የታገለው ለሥልጣን ነው የሚሉ ክፍሎች የወነጀሉ ያጋለጡ ከመሰላቸው ተሳስተዋል። የፖለቲካ ትግል ማሰሪያው፥ መዳረሻው የፖለቲካ ሥልጣን ነው። ሌላ አይደለም። ዛሬ ከወያኔ የምንታገለው ወያኔን ለማስወገድና ሥልጣን ለመያዝ ነው። ይህ በአደባባይ የምንናገረው የፖለቲካ ሀሁ ስለሆነ ኢሕአፓ ለሥልጣን ታገለ ብለው ሊነቅፉ የሚነሱት ስለምን እንደሚያወሩ አልገባቸውም ብለናል። ኢሕአፓ ለሥልጣን ሲታገል ግን ከሌሎች የሚለየው ወይም ይለየኛል የሚለው ነጥብ-፥- እንበል ለምሳሌ ከደርግና ወያኔ ቡድን የሚለየው-- ሥልጣኑን ለራሱ በቡድን በድርጅት ደረጃ ይዞ ሕዝብ ላይ ለመሰየም ሳይሆን፥ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት እንዲሆን በማድረግ ነው። ማለትም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማስፈን። ሕዝብን ባለሙሉ መብት በማድረግ። መንግሥት የሚሆነው አካል፥ ሥልጣኑን የሚያገኘው በሕዝብ ነፃ ምርጫ ብቻ እንዲሆን በማድረግ። ሕዝብ ያልፈለገውን መንግሥት የማውረድ መብት እንዲኖረው በማረጋገጥ። ለዚህ ነው ኢሕአፓ የሚታገለው። ሥልጣን ግን ካልተያዘ፥ ወይም ሕዝብ ወሳኝ ፥ ይህን የተፈለገ ለወጥ ለማምጣት አይቻልም ስለዚህ ጨቋኙን አስወግዶ ሕዝባዊ ሥልጣንን ማስፈን የግድ ነው። በየካቲት 66 ዴሞክራሲያዊ መብት ለሕዝብ አለምንም ገደብ ብሎ ኢሕአፓ ከደርግ ጋር ተጋጨ እንጂ፥ ሹመትና ሥልጣን ካካፈልከን፥ ባፈተተህ ጨቁን፥- ገድብ ብሎ ሕዝብን እንደ ሌሎች አልካደም። ስለዚህም ባለፈው ታሪካችን፤ በወሰድናቸው ተጨባጭ አቋሞች ሕዝብ ሊገመግመንና ለግል ወይም ድርጅታዊ ሥልጣን አለመቆማችንንም ሊመሰክር ይችላል። ሥልጣን ለራሴ ያሉ*

ኢሕአፓዎች ድርጅቱን እየከዱ፥ አንዴ ለደርግ፥ ለጥቆም ለወያኔ በግላቸው አደሩ እንጂ፥ ድርጅቱ ለሕዝብ ከገባው ቃል ኪዳን ወደ ኋላ አላለም። አልካደም። አባሎቹ ደግሞ የትግል ቤታቸው ነውና ተንከባክበው ጠብቀውታል፤ወደፊትም ይይዙታል። ድርጅታቸውን የሚያፈቅሩትም ለሀገርና ለሕዝብ ስለቆመ እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም። ይህ በመሆኑም ድርጅቱን ሲያስቀድሙ ሀገርን ወይም የሕዝብን ጥቅም ያስቀድማሉ ማለት ነው። ኢሕአፓ የሕዝብና የሀገርን ጥቅም አሳልፎ ቢሰጥ፥ በመጀመሪያ ደረጃ አባሎቹ አብረውት አይኖሩም። በአባላቱ ፅናትና ድርጅታዊ ፍቅር የሚረበሹ ክፍሎች ናቸው፥ ይህንን ፅናትና ፍቅር ሌላ ትርጉም ለመስጠት የሚፈልጉት።

<u>ጥያቄ፡-</u> ኢሕአፓ በሰላማዊ ትግል አያምንም ነበር። በደርግ ላይም ተሽቀዳድሞ ተኩስ የከፈተው ለዚሁ ነው የሚሉ አሉ። ይህ ሀቅ ነው?

<u>መልስ፡-</u> ኢሕአፓ ለትጥቅ ትግል የተዘጋጀው የአፄው ሥርዓት፥ ለሰላማዊ ለውጥ በሩን ሁሉ ዘግቶ በነበረበት ጊዜ ነው።ደርግ የሕዝብን ትግል ፍሬ ቀምቶ ሥልጣን ሲይዝ ደግሞ ያለውን አዲስ ሁኔታ በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል መለወጥ ይቻል ይሆን ብሎ ሞክሮ ነበር። በሜዳ የነበረ ኃይሉን እንኳን በይፋ ሳያውጅ ጊዜ ከመፍጀቱ ሌላ ባወጣው የፖለቲካ ፕሮግራም መግቢያም ላይ፥ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ መታገል ከተቻለ፥ በዚሁ መንገድ እንታገላለን ብሎ ነበር። ከዚያም ሌላ አላደረገም። በፅሁፍ፤በቅስቀሳ፤በየቀበሌው በመሰለፍ ወዘተ ነው የታገለውና ሕዝብን ያደራጀው።ኢሕአፓ ሕዝብን ለትግል በፅርግጥ አነሳስቷል--ለዚህ ደግሞ ማንንም ይቅርታ አይጠይቅም። ወታደራዊው መንግሥት ህገ ወጥ ነው ብሏል፥ ሀቁ ይህ ነበር።ጭቆናና ባለበት አመፅ መወለዱ ደግሞ በቅድሚያ ተጠያቂ የሚያደርገው ጨቋኞቹን ነው እንጂ የግፍ ሰንሰለትን ሊሰብር የሚመኘውን ሕዝብ አይደለም። ነሐሴ 21/1967 ዓ/ም በወጣው የኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ዕትም ድርጅቱ አቋሙን ሲገልጥ የሚከተለውን አስፍሮ ነበር።

"የጥቂት አምባገናናዊ መኮንኖች መንግሥት ተነስቶ <u>በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መተካት አለበት</u>።ለዚህም አብዮቱን ጀምረው ያካሄዱትንና የደገፉትን፤ወደፊትም ሊያካሂዱት የሚችሉትን የህብረተሰብ መደቦችና ኃይሎች የሚወክል ሕዝባዊ አብዮታዊ ሸንጎ መቋቋም አለበት።" ካለ በኋላ የሸንጎውን ይዘተ በተመለከተም በዝርዝር አስፍሯል። በዚሁም ሰነድ ደግሞ የኤርትራ ጉዳይ ሀገርን እየጎዳ ያለው ጦርነት ቆሞ በዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ መንገድ መፈታት አለበት ብሎ በጊዜ ጠቁሞና አሳስቦ ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን፥ ሌሎችም ኃይሎች በትግል ላይ እንደነበሩ በመገንዘብ፥ በመነሻ የፖለቲካ ፕሮግራም መሠረት፥ ተቃዋሚ ኃይሎች እንዲተባበሩና ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ የህብረት ግንባርም እንዲመሰርቱ ጥሪ አድርጎ ነበር። በዚህ መልክ ነበር የታገለው ኢሕአፓ። ዛሬ የሰላማዊ ትግል ትርጉም የጠፋቸው ክፍሎች፥ አንድ ድርጅት በሥልጣን ያለውን ኃይል ይውረድ ካለ፤ ለማውረድም ሕዝብን ካደራጀና ካታገለ፥ ሰላማዊ ትግልን የተወ ይመስላቸዋል። ሰላማዊ ትግል ማለት፥ ጠባይን አሳምሮ ለገዢው ቡድን ታማኝ ተቃዋሚ መሆን እየመሰላቸው ነው። ስህተቱ ከእነሱ እንጂ ከኢሕአፓ አይደለም። የመኮንኖቹን ቡድን ኢሕአፓ በትግል አስጨንቋል፤ አራውጧል። በፖለቲካው ትግል መስክም አሸንፎም ነበር ማለት ይቻላል። ስለተሸነፉም ጦርነት አወጁበት። ኢሕአፓ በከተሞች አንዲትም ጥይት ከመተኮሱ በፊት፥ ደርጉ በሕዝብ

ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ላይ፤ በኢሕአፓ አባላት ላይ፤ በተቃዋሚዎች ላይ፤ በተቃዋሙ ወታደሮችና መኮንኖች ላይ፤ በአርሶ አደሮች ላይ ወዘተ በአዲስ አበባም በክፍለ ሀገርም የግድያ እርምጃ ወስዷል:: ቀይ ተብሎ ገና ያልተሰየመ ሽብር ይካሄድ ነበር:: አሁን ተፈላጊው የዲሞትፎር ጥይት እንጂ÷ ዴሞክራሲ አይደለም ብለው ያጓሩት መኮንኖችና አማካሪዎቻቸው በኢሕአፓ ላይ በይፋ ጦርነት እስኪያውጁ ድረስ ግን ከግድያ አልተቆጠቡም ነበር:: ይህን ሀቅ የሀገራችን ሕዝብ በግልፅ ያያውና የሚያውቀው ነው:: ኢሕአፓ የመከላከል እርምጃ መውሰድ የጀመረው ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው:: ዛሬ የቀድሞው ደርግ መሪዎች፤አማካሪዎቻቸውና ምስክሮቻቸው÷ ሌላ ቢያወሩ ይህ የማይደበቅ ሀቅ ነው:: በሰላም የታገላቸውን ሕዝብና ድርጅት ሊያጠፉ አሲረው ጦርና ነፍሰ ገዳዮች አሰማርተው ፍጅት አካሂደዋል:: ዛሬም ያን ፍጅትና ወንጀል ክደው ተጠቂውን ኢሕአፓ÷ የሚወነጅሉት ያው ባደቆናቸው ስህተትና ጥፋት ሲቀጥሉ እንጂ ከሀቅ ሲታረቁ አይደለም:: ወያኔም ለሥልጣን ሲበቃ ኢሕአፓ በሰላም ለመታገል ያለውን ፍላጎት በይፋ አሳውቆ ነበር:: የወያኔን አሉታዊ ምላሽ ግን ሕዝብ የሚያውቀው ነው:: አሁንም ቢሆን ኢሕአፓ÷ በህብረት ከሌሎች ጋር ሆኖ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ያለውን ፍላጎት ያደናቀፈው የመለስ ቡድን ነው::

<u>ጥያቄ፡-</u> የኢሕአፓና የደርግ መኢሶን ሆነ ከወያኔ ጋር ያለው ጠብ የፕሮግራም ሳይሆን÷ የሥልጣን ሽሚያ ነው የሚሉ አሉ:: ይህ ዕውነትነት አለው?

<u>መልስ</u>፡- አንድ ትልቅ የአብዮት መሪ የነበሩ ሰው÷ “ያላነበበና ለማወቅ ያልጣረ የ ግግርና የትችት መብት ሊኖረው አይገባም” ያሉትን ያስታውሳል ይህ ክስ::ደርግም ፤መኢሶንም÷ ኢሕአፓም የግራ ክንፎች ነበሩ ቢባልም አቋማቸውና ፕሮግራማቸው አንድ አልነበረም:: ያነበበ ሊረዳው ይችላል:: አንዳንድ ፀረ ግራ የቀኝ ኃይሎች ግን እሳት ካየው ምን ለየው ይሉና ሁሉም ያው ናቸው በማለት በስንፍና ደምድመው ያሳስታሉ:: ሌላውን ግን ማሳሳት አይችሉም:: ለነገሩ የዓለም አድህሪና ቀኝ ኃይሎች አንድ አይደሉም:: ካፒታሊስት ስለተባሉ በኖርዌይና አሜሪካ፤ በፈረንሳይና በጣሊያን ያሉት ሥርዓቶች÷ ወይም ኃይሎች አንድ ወጥ አይደሉም:: በደርግና በኢሕአፓ መሀል የማይታረቅ መሠረታዊ ልዩነቱ ብዙ ነበር:: በኢሕአፓና በወያኔ መሀል ገና ወያኔ ትግራይ ተገንጥላ ሌላ ነፃ መንግሥት ትሁን ካለበት ጊዜ ጀምሮ÷ በሀገር ጉዳይና በሕዝብ መብት ጉዳይ መሠረታዊ ልዩነት ለግጭትም ያበቃ ቅራኔ ነበር:: ዛሬም አለ :: ስለዚህ ግጭቱ በመሠረታዊ የፖለቲካ÷ የአቋም ልዩነት እንጂ÷ በባዶ አልነበረም፤ አይደለምም :: ዛሬም ቢሆን በድርጅቶች መሀል ያሉት ልዩነቶች ተወግደው በህብረት ተያያዙ የሚል ጥሪ ቢኖርም÷ በድርጅቶች መሀል ያሉ የአቋም ልዩነቶች ሊካዱ አይገባም:: ዋናው ትኩረት መሠረታዊ ባልሆኑ ልዩነቶች መለያያትና መቃቃር አይገባም በሚለው ላይ ነው:: ዋና ትኩረት ሀገር በአደጋ ላይ ስለሆነች÷ እሷን በማዳን ላይ ሆኖ÷ የፕሮግራም ልዩነት ዋና ቦታ አይሰጠው ለማለት እንጂ÷ የማይናቁ የአመለካከትና የአቋም ልዩነቶች ዛሬም አሉ:: ኢሕአፓ ትመስረት የሚላት ዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ኢትዮጵያ÷ ሌሎች ከሚሉትና ከሚፈልጉት የተለየች ልትሆን ትቾላላች:: መስማሚያው ዋና ነጠብ ግን÷ በጋራ÷ የመለስን አገዛዝ ማስወገድና ሕዝብ የትኛው ይበጃል ብሎ እንዲመርጥ መብትን ማረጋገጥ የሚለው ላይ ሊኖር የሚገባው ስምምነት ነው:: ደርግ ለምርጦች ወታደራዊ አምባገነንነት ሲቆም ኢሕአፓ ለሕዝበዊ ሥልጣንና

ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ነበር የየቆመው:: መኢሶን ከደርግ ጋር በሂሳዊ ድጋፍ ማበር ሲል፥ ኢሕአፓ ይህን አማራጭ ተቃውሟል:: ወያኔ፥ የብሄረሰብ ቅራኔ ዋናው ነውና ሁሉም ተገንጥሎ የየራሱን ነፃ መንግሥት ይመስርት፥ ወዘተ ሲልም፥ ኢሕአፓ የጭቁኑ ህዝብ መብት በተከበረባት ኢትዮጵያ፥ አብሮ መኖር ይፈልጋል፤ ይቻላል ወዘተ ብሎ ግልፅና ጥርት ባሉ አቀሞች መሰረት ተለይቶ ቆይቷል:: ዛሬም የኢሕአፓና የወያኔ ፕሮግራም ለየቅል መሆናቸውን ማንም ሊረዳ ይችላል::

<u>ጥያቄ:-</u> ሌላ በደርግ ተጀምሮ እስከዛሬ የሚስተጋባ ክስ ደግሞ፥ ኢሕአፓ የሶማሊያን ወረራ ደገፈ ፤የሶማሌውን መሪ ዚያድ ባሬን ቪቫ ብሎ ደገፈ፤ሀገርን ከዳ፤ ጦሩን ከፋፈለ ፤በታጠቅ ጦር ሰፈር ይሰለጥን የነበረውን ሚሊሺያ ጠርሙስ ፈጭቶ በምግብ ጨምሮ ፈጀው ወዘተ ወዘተ የሚሉ ናቸው:: ለዚህስ ምን ምላሽ አለ?

<u>መልስ:-</u> ኢሕአፓ የሶማሊያን ወራሪ ጦር ደገፈ ብሎ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የዋሸውን፥ የወያኔው የውሸት አባት፥ ስብሀት ነጋም፥ ከአዲስ አበባ ሲያስተጋባ ተደምጧል:: በሞቃዲሾ ቢሮ ከፍቶ፤ በዚያድ ባሬ በሁሉም መስክ እስከመጨረሻው ተደግፎ፤ ከሀረርጌ እሰከ ባሌና አደማ ናዝሬት ድርስ፥ የምዕራብ ሶማሌ ግዛት ነው ብሎ የፈረመው የወያኔ መሪ፥ እንግዲህ ይህን ሁሉ የሚያውቅ የለም ብሎ ሲቀጥፍ ሰማን ማለት ነው:: ውሽታሞች--በተለይም የለመደባቸውና በሥልጣን ያሉ ቀጣፊዎች፥ ለከትም፥ ገደብም እንደሌላቸው በመንግሥቱም፥ በመለስም፥ በስብሀትም አይተናልና ብዙም አያስገርምም:: በኦጋዴኑ ጦርነት ጊዜ ግን፥ ኮለኔል መንግሥቱና ጭፍሮቹ፥ ኢሕአፓን ለማጥፋት ሽብር እያካሄዱ ነበሩና፥ ኢሕአፓ፥ ዚያድ ባሬን ወይም ሶማሊያን ደገፈ ብለው መዋሸቱ ድጋፍ ለማግኘት -በተለይም ከወታደሩ ክፍል- ይጠቅመናል ብለው ዓይናቸውን በጨው አጥበው የጀመሩት ውሸትና የሀሰት ቅስቀሳ ነበር:: ማንም ቢሆን ማን፥ አሉባልታን ከማናፈስ ሌላ፥ ኢሕአፓ ወረራውን ደገፈ ብሎ ማስረጃ ማቅረብ አልቻለም:: ይህም የሆነው ድርጅቱ ወረራውን ያልደገፈ በመሆኑ ነው:: ኢሕአፓ በኦጋዴን ያለው ኢትዮጵያዊ የብሄረሰብ በደል ይደርስበታል ብሎ በአጠቃላይ አቋሙ መሠረት፥ ዕምነቱን የገለጠ ቢሆንም፥ የተጨቆነ ሕዝብ ትግልና፥ የባዕድ ሀገር ወረራ አንድ አለመሆናቸውን ጠቁሞ፥ ወረራውንና ሁለቱንም ሕዝቦች የሚያጫርሰውን ጦርነት አውግዟል:: የዚያድ ባሬ ወረራም፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፀረ ደርግ ትግል የሚያደናቅፍ መሆኑንም ጠቁሞ ተቃውሞታል:: በዴሞክራሲያ ቅፅ 4 ቁጥር 9 የሰፈረውን የኢሕአፓን አቋም መረዳት ያቃታቸው ደግሞ፥ ያውም የዘቀደ አሉባልተኞች አንበውት ከሆነ ፥ “ደግፏል! ደግፏል!” ብለው መቀጠሉን የመረጡ ይመስላል:: ኢሕአፓ፥ በወታደሩ ውስጥ ለማደራጀት እንደጣረው ሁሉ፥ በሚሊሺያውም ዘንድ ተንቀሳቅሷል:: የጠርሙስ መፍጨት አስቂኙን አሉባልታ ትተን ማለት ነው:: ጦርነት መንስዔው ምንድ ነው፤ ጠቀሜታውስ ለማን ነው ብሎ መጠየቅ ግዴታ ነው:: አለበለዚያ ጨቋኝ ገዢዎች ሕዝብን ሁሌ ጀሌና ጥይት ማብረጃ፤ ቅራኔን ማርገቢያ ያደርጉታል:: ይህንን በተመለከተ፥ ወያኔና ሻዕቢያ ለጦርነት ሲያቆበቁቡም ኢሕአፓ ጠቁሞ፤ አሳስቦና አስረድቶ ነበር:: መላ ኤርትራን ትገንጠል ያለና የተባባረ ቡድን፥ ድንገት በአንዲት ባድሜ የተነሳ፥ ሀገር ወዳድ አይሆንም ብሎም፥ ኢሕአፓ ከመጋረጃው በስተጀርባ፤ የመለስ ቡድን፤ ሀገራችንን እናድን የሀሰት ጥሪ በስተጀርባ ያለውን ሴራ አጋልጦ ነበር:: ሻዕቢያና የኤርትራ ሕዝብ አንድ አይደሉምና፥ በኢትዮጵያ በነበሩ

ኤርትራውያን ላይ የወሰደውንም የገፍ ማባረርንም ተቃውሞ ይዘቱንም አጋልጧል፡፡ መግለጫም አውጥቷል፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ ሻዕቢያን በመደገፍ ወይም ኢትዮጵያ ትወረር በማለት ሳይሆን፥ የገዢውን ቡድን ሴራ በማወቅና በመቃወም ሀገርንም መጠበቅ ገዢውንም ቡድን በገባባት ቀውስ ተጠቅሞ ማስወገድ ይገባል በሚል ነው፡፡ የለም፥ በደፈናው ለእነ መለስ ጥሪ ድጋፍ እንስጥ ያሉት ደግሞ ያ ሁሉ ህይወትም ጠፍቶ፥ ባድሜ ብቻ ሳትሆን፥ አዲ ኢሮብም፥ ለሻዕቢያ ተፈርዶለት፤ የተባረሩ የተባሉትም እየተመለሱ፤ የተሰዉት ቤተሰቦቻቸው ጧሪና ተንከባካቢ አጥተውና፥ መለስም ከእነ ጭፍሮቹ ዛሬም በቤተ መንግሥት ሲፈነጭ ይገኛል፡፡ለዚህም ነው ገዢዎች፥ ሕዝብን ተነስ ሲሉት፥ ለምንና ለማን ጥቅም ብሎ መጠየቅ የግድ ይላል፡፡ በአምባገነን ሥርዓቶች፥ ሀገርና፥ ቤተ መንግሥት የተሰየመ ቡድን አንድ ጥቅም የላቸውም ፡፡ አለበለዚያማ ወሮበሎች ሁሌም በሀገር ወዳድነት ጥሪ ዙሪያ ይደበቃሉ የተባለውን መዘንጋት ይሆናል፡፡ ዛሬ የሻዕቢያ ተቃዋሚዎች የጦርነት ዝግጅትን አውግዘው ኤርትራዊ ከኢትዮጵያዊ የሚያፋጅ ቅራኔ የለውም ብለው ለሕዝብ አንድነት ወይ ሰላም ቢቀሰቅሱ ሊወገዙ ነው? ገዢ ቡድኖች፥ የሕዝብ ትግል ሲያይልባቸው ፥ የውጭ ጠላት መጣብህ ብለው በሀገር ፍቅር ሰበብ የሕዝብን ዕይታና ትኩረት ከእነሱ ላይ እንደሚያነሱ የታወቀ ነው፡፡ ይህ እንዳይሆን መታገል ያሻል፡፡ ኢሕአፓ እንደ ድርጅት ሀገር ሲል ሕዝብን ረስቶ አይደለም፡፡ ከዚህ ሌላ ግን፥ በዚያድ ባሬ ወራሪ ጦርም ሆነ፥ ኋላም በሶማሊያ በስደት ላይ፥ መከራ የተቀበሉና የተሰዉም የኢሕአፓ አባላት ቁጥር ጥቂት አልነበረምና፥ ኢሕአፓን፥ በዚያድ ባሬ ደጋፊነት ለመክሰስ መሞከሩ፥ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ይሆናል፡፡ ኢሕአፓ ከዚያድ ባሬ ጋር ልክ እንደ ወያኔ አብሮና ግማሽ ኢትዮጵያን የሶማሌ መሬት ብሎ ፈርሞ ቢገኝ ኖሮ፥ በዚያድ ባሬና መሰሎቹ ሙሉ ድጋፍ፥ ዛሬ እንደ ወያኔ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ቀንበር በሆነ ነበር፡፡ ይህ ግን የኢሕአፓ ሳይሆን፥ የእነ ወያኔ ሰልፍና ምርጫ መሆኑን ጊዜ በሚገባ አሳይቶናል፡፡

ጉዳዩን ጠለቅ ብለን ከመረምርን ደግሞ፥ ትላንትም ሆነ ዛሬ፥ በኢሕአፓ ላይ መሰል ክስ የሚደረድሩት፥ በአብዛኛው ራሳቸው ለባዕድ ወይም ለሀገር በቀል አልባሌ ኃይል፥ ተገዥ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ወያኔ፥ ለሱዳንም፤ ለሻዕቢያም፤ ለሊቢያም ሆነ ለሁሉም ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ቅጥረኛ ነበር፡፡ ዛሬም አልተለወጠም፡፡ የደረግ መኮንኖች ሀገሪቷን ለሶቭየተ ህብረት አሳልፈው ሰጥተው ነበር፡፡ ዛሬ ተለጣፊ የሚባሉት ቡድኖች የመለስ ዜናዊ ሎሌዎች ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ኃያል ለተባለው መንግሥት፥ ደፋ ቀና ሲሉ እንታዘባለን፡፡ ይህ ሁሉ፥ ከኢሕአፓ መንደር አይታይም፡፡ ኢሕአፓ ለማንም መንግሥት ወይም ኃይል ተገዢ ሆኖ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ሰጥቶ አያውቅም፡፡ ለጥቅም ሲል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጨቋኞች ጋር የሥልጣን ቅርጫ ውስጥ አልገባም፡፡ ይህን አሌ የሚልና በሀቅ የሚደገፍ ማንም የለም፡፡

ይቀጥላል.....

ታሪክን የሚረሳ ስህተትን ይደግማል ተብሏል። ያለፈውን በማስታወስ የቂም በቀልን ቁስል ለማመርቀዝ አይደለም። ወያኔና መሰሎቹ የአፄ ምኒሊክና የነፍጠኞች ወንጀል በሚል ሕዝብን በመጥፎ ሊበክሉና እርስ በርስ ሊያጣሉ ሲጥሩ ታዝበን ነበር። እነ አሶሳ፤ በደኖና አርባጉጉ ናቸው የፍጅት ውጤቶች። ከታሪክ ግን ጥሩ መማር ይቻላል--ያኔ ታሪክ ገንቢ ቅርስ ይሆናል። ራሳቸው አነገብነው የሚሉት የቀኝና የበዝባዥ ርዕዮት ማጠየቂያው ከፈረንጁ ያልሆነ ይመስል÷ ለሕዝባዊ ለውጥና ለሀገር ሲል የታገለው ያ የየካቲቱ ጀግና ትውልድ ለባዕድ ርዕዮት እጅ ሰጠ ብለው የሚቱቱት ክፍሎች ያልገባቸው ነገር ቢኖር÷ ታጋዩ ትውልድ የወጭ ወራሪን ታግለው በአርበኝነት የሙሶሊኒ- የጣሊያንን ጦር መመለሳቸው ምንኛ እንደቃኘው ነው። ያለፈው ታሪክና ጀግንነት አዲሱን ትውልድ ጀግና አድርጎታል። ያን የየካቲቱን ትውልድ ገደል ግን ከአፄውም ከደርጉም አብረው በልተው ከወያኔም ማዕድ የቀረቡ የታሪክ አተላዎች ሲያጎድፉት እየታዘብን ነው። መስዋዕትነተንና ፅናትን ስለሚያክቸለችሉ ለሀገር መታገል ሞኝነት ወይም የከተማ ወጣቶች እንደሚሉት ፋራነት ሆኖ ሆድን ማስቀደም፤ግለኝነትን ማንገስ ግን ብልህነት ተባለ። የሀገርም ዋጋዋ ረከሰ፤ በጎ ባህል ተንቆ የባዕዱ ብልሽት ታቀፈ ። በስልጣን ያለው ቡድን ደግሞ ባለጌ፤ዋልጌ፤ በሙስና የተጨማለቀና ስነ ምግባር የሌለው በመሆኑ የድንጋይ ሀውልትን አክሱም አስገባሁ ሲል በሌላ በኩል ደግሞ የሀገርን ታሪክ በመቶ ዓመት ወስኖና በርዞ ላመጥፋትና ሕዝብን ቅርስ አልባ ለማድረግ ባለው አቅሙ ይፍጨረጨራል። የኢሕአፓ የትግል ታሪክ የሕዝብ ቅርስ ነው። ጀግኖች የደሙለት፤የተሰዉለት፤ መከራ የተቀበሉለት ታሪክ ነው። ልጆቿ በቀይ ሽብር የተፈጁበት ወላጅ፤ ወንድም እህቱ በቀበሌ ና በማዕከላዊ፤በደርግ እስር ቤቶችና ማጎሪያዎች በስየል ተጠብሰው የሞቱበት ሁሉ፤ የሰራተኛው ቀን ሰማዕት፤ የተረሸነው ሰርቶ አደርና የብቸናና ሌሎች ቦታዎችም አርሶ አደር ወገኖች ወዘተ ወዘተ ሁሉ የዚህ ታሪክ ባለቤተ ናቸው። ሕዝብ ሞቶ አያልቅምና ይህ የጀግኖች ታሪክ ደግሞ በከይሲዎች ተበርዞ ከቶም ሊጠፋ አይችልም። ይህንንም ለማረጋገጥ በበኩላችን ማን ያውራ የነበረን በመቀጠል ሀቁን ማስፈሩን ተያይዘነዋል።

ጥያቄ-- ኢሕአፓን ወጣቱን አስጨረሰ የሚሉ ከሳሾች አሉ። ለዚህ ድርጅቱ ምን መልስ ይሰጣል?

መልስ-- ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው ማለት ይቻላል በመጀመሪያ። ትግል የቀሚስ ጥበብ አሳምሮ መስፋት ዓይነት አይደለም። የመደቦች ግብግብ ነው፤ ጥቅሞች የሚፋጩበትና አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ የሚዋደቅበት ነው። ስለዚህ አለ መስዋዕትነት ትግል የለም። የደላቸው ሀገርስ ላም ነው ሲሉ በዚያኑ ወቅት ደግሞ ያልደላው እየተሰቃየ እየሞተ እንዳለ ማወቅ ያሻል። ዛሬ በእነ መለስ ነገድ ሼራተኖች በጅምላ ሲፈነድቁና ሲደሰቱ ብዙ ሺዎች ደግሞ የሚበሉት አጥተቅ በመንገድ አዳሪ ሆነዋል። ወንጀሉና ግድያው ቀጥሏል ማለት ነው። ይህ ያብቃ ብሎ ሕዝብ ሲነሳ የእነ መለስን በራ ሊዳስስና በፍቅር ሊይዛቸው መጠበቅ የለበትም። የመለስ መንጋም ቢሆን አፉን ሲከፍት ለፈገግታ ሳይሆን የእባብ መርዙን በሕዝብ ላይ ሊተፋ ነው። ገዢ መደብ ወይም ቡድን በሰላም አለትግል ስልጣኑን አይለቅም--ቢያንስ በኢትዮጵያ ልናየው ያልታደልነው ክስተት ነው። ስለዚህም ለውጥን የሚፈልግ ሕዝብ ለትግልና ለመስዋዕትነት መዘጋጀት አለበት።

ኢሕአፓ ውድ አባላቱን ሙቱ ብሎ በግድ የለሸነት አልማገደም። መሪዎቹ አባሉን በዚህ መንገድ ጎዱት እንዳይባል ደግሞ የኢሕአፓ አመራር አባሎች ለመስዋዕትነቱ ግንባር ቀደም ሆነው አልፈዋል። ወያኔን ሲታገሉ እንኳን የተሰዉት ወይም ተይዘው ደብዛቸው የጠፋው ጥቂት አይደሉም። ድርጅት ከታገለ መስዋዕትንት ይከፍላል። ካልታገለና ጠባይ አሳምሮ ገዢውን ሳያስቆጣ ከቀጠለ ደግሞ የሚደርስበት አደጋ አይኖርም--ግን ታገልኩ ቢል ዛሬ እንደምናያቸው አንዳንድ ተቃዋሚ ነን ባይ የሱቅ በደረቴ የአንድ ወይ ሁለት ሰው ቡድኖች መሳቂያ ይሆናል። ድርጅት ሲታገል አለአቅሙ ነው። መንግስት ስልጣን የጨበጠ ቡድን በገንዘብም በጦር መሳሪያም የደረጀ ነውና። የጣሊያን ወራሪ ጦር በዘመናዊ መሳሪያ የደረጀ፤ ተዋጊ አይሮፕላን የነበረውና የመርዝ ጢስ የመበተንም አቅም የነበረው ነበር። በጦር፤በጋሻ፤ በቃታ ብረት ነው አርበኞች ጠምደው ምሱን ያቀመሱት። ኃያሉ ፈረንሳይና አሜሪካም በቪየትናም ሽንፈትን ቀምሰዋል። ኃይል የሕዝብ ነው ግን ይህ በመራራ ትግል እስኪረጋገጥ ጠላት የሆነው ወራሪ ወይም ጨቋኝ ኃይል አለውና ትግል የሚገጥመው ድርጅተና ሕዝብ ቢያንስ በአቅም ጊዜያዊ ድክመት ይታይባቸዋል። መጋፈጥ ይገደዳሉ ማለት ነው። ተማሪዎች መሬት ለአራሹ ብለው ሲሰለፉ ዱላም ሌላም ቀምሰዋል። ከዱላ ወደ ጥይትና ህይወት ማጣትም ተኪዷል። አለአቅማችሁ የሚሉ፤ አሁን ድህ ተማሪ ጃንሆይን ሊጥል እያሉ የሚያሾፉ ነበሩ። በደርግም ጊዜ የተለየ ክስተት አልነበረም። በአጭሩ ሊታገል የተነሳ ድርጅትና ህዝብ መስዋዕትነት አይቀሬ መሆኑን ማወቅ አለበት ማለት ነው።

ኢሕአፓ ትገሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ከፍሏል። ታጋለ አታገለ እንጂ አላስጨረሰም። ራሱ በግለ ሂስ መልክ ከዓመታት በፊት እንደገመገመው ግን በከተሞች ይካሄደ የነበረውን ትጥቃዊ እንቅስቃሴ የኃይል ሚዛ ለውጥ ግልፅ ሲሆን ማቆም ነበረበት ማለት ይቻላል።በጦር ሜዳ አዋጊ የሆነ አዛዥ ስህተት ሊፈፅም ይችላል። የሀገሬ ሰው የመንደር አውደልዳይ የሚለው በጦር ሜዳ አይውልምና ስህተት አይፈፅምም። ኢሕአፓ አዲስ ድርጅት ስለነበረና ከእሱ በፊት ሌላ ታጋይ ድርጅት ኖሮ ከዚያ ተመክሮ በወጥታ ሊማር ባለመቻሉ ስህተቶችን ፈፅሚል። የትግል የታጋይ ስህተት። ቸኮለ ከተባለም ለትግል እንጂ ለፓርላማ ወንበር አልነበረም። ደፈረ ቢባል ሹመት ለመቀበል ሳይሆን ጨቋኙን ለመታገል ነበር። በዚህም የትግል ሂደት ኢሕአፓ ባዕዳንንም ያስገረመ ታሪክ ፅፏል። ዛሬም የመለስን ቡድን አለ መስዋዕትነት እናስወግዳለን የሚሉ ካሉ ደግሞ ይህን ተዓምር ለማየት ዕድሜ ይስጠን ማለት እንችላለን።የማይሆን ነገር ነው። ለነገሩ ወያኔም ሻዕቢያም ዓላማቸውን ባንደግፈውም ከደረሱበት የደረሱት ዋጋ ከፍለው ነው።

ጥያቄ-- ኢሕአፓ ግን አላሸነፈም ከሚል ተነስተው ይሆናል የሚተቹት

መልስ-- ስልጣን ከመያዝ አንፃር በእርግጥ ኢሕአፓ ለስልጣን አልደረሰም። ግን ኢሕአፓ ብዙ ድሎችን ተቀዳጅቷል። የሕዝብ ትግል ማየሉና ከዚህ መድረሱ ራሱ ከኢሕአፓ የዓመታት ትግልና ነቃትን ለማዳበር ካደረገው ያልተቋረጠ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው። ኢሕአፓ ለራሱ ስልጣን ፈልጎ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው በሚል ታግሎ በነበር ደግሞ በሱዳንም፤በሶማሊያም፤በአረብ ሀገሮችም ሆነ ባባዕዳን በአጠቃላይ ተደግፎ--ማለትም ለእንሱ አድሮ--ለስልጣን በበቃ ነበር። ኢሕአፓ የትግል ትምህርት ቤት ነበር፤ዛሬም ነው። ኢሕአፓ ያስተማራቸውና የቃኛቸው ናቸው ዛሬ መስመር ቀይረው ቢበላሹም የፖለቲካ ሀሁን ጨብጠው ሌሎች ድርጅቶችን አካሂያጅ የሆኑት። የኢሕአፓ ትውልድ የዘመናዊ ፖለቲካ ፅንስ

ሀሳቦችን፤ የሕዝብን ወሳኝነት መርህ፤ የድርጅትን አስፈላጊነትና ስልት፤የእኩልነት መብት ወሳኝነትን ወዘተ ከሕዝብ ያስተዋወቀ ነው፡፡ የኢሕአፓን አደረጃጀትና ትግል በጥሞና የሚመረምሩ ብዙ ሊማሩ ይችላሉ፡፡ ዛሬ አሸንፍኩ ባዩ ወያኔ ተሸነፈ የሚለውን ኢሕአፓን የሚፈራው ለምን ነው ብሎም መጠየቅ ያሻል፡፡

ጥያቄ-- ኢሕአፓ ሕዝብ አስጨርሷልና ሕዝብ ይጠላዋል የሚሉም አሉ፡፡ ከዚህም ተነስተው ስሙን ይለውጥ ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ኢሕአፓ ለዚህ መን መልስ አለው?

መልስ-- የኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢሕአፓ ፍቅርና አክብሮት እንጂ ጥላቻ የለውም፡፡ የጭቆና አገዛዝ የግልፅና የስውር ጠበቆች በእርግጥ ኢሕአፓን ለማስጠላት ትላንትም ዛሬም ሲደክሙ እናያለን፡፡ ለዚህም ነው ኢሕአፓ ያለረገውን አረገ ብለው ሲዋሺ የሚደመጡት፡፡ ኢሕአፓ ለሕዝብ ብሎ የታገለ የሕዝብ አገልጋይ የነበርና የሆነም ድርጅት ነው፡፡ ሕዝብ ጠላቴ የሚላቸው ናቸው የኢሕአፓ ጠላቶች፡፡ ሕዝብ ወታደራዊውን መንግስት ጠላው ታገለው--ኢሕአፓ ከጎኑ ቆሞ ተሰዋ፤ትግሉን አስቀጠለ ፡፡ የወያኔን መንጋ ሰፊው ሕዝብ አምርሮ ጠላው- ይህን ገንጣይ ቡድን ኢሕአፓ ዛሬ ጅብ ከሄደ እንዲሉሰ ሮይሆን ገና በደደቢት ዳዴ ሲል ጀምሮ ታገለው፡፡ የሕዝብና የኢሕአፓ ፍላጎት አንድ ነው፡፡ ከሕዝብ ፈላጎት የተጣላ ዓላማ ኢሕአፓ ሊኖረው አይችልም፡፡ በስሙ ውስጥ ሕዝባዊ ሲል በባዶ አይደለም፡፡ ኢሕአፓ የሚለው ስም የትግል መለያ፤የሚያኮራና ቋላትና ቅጥረኛችን የሚያባንን ስም በመሆኑ ለምን መቀየር እንዳለበት ለኢሕአፓ ግልፅ አይደለም፡፡ ይቀየር ባዮች ብዙዎቹ ከስሙ  ጋር ያለውን ታሪክ ለመፋቅ ለመሰረዝ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ቢያንስ ይህን ማድረግ ከትግሉ አንፃር አስፈላጊ እስካልሆነ ድረስ፡፡ ኢሕአፓ በህብረት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሲተሳሰር ህልውናው ባያከትምም በጋራው ስም ዙሪያ ነው የታገለውና ዛሬም እየታገለ ያለው፡፡ ለነገሩማ ወያኔም ኢሰፓም ስም ሆነው ዛሬም ኢሰፓ ነን፤ወያኔ ነን የሚሉ አሉ አይደል!

ጥያቄ-- የህብረት ጥያቄ ከተነሳ አይቀር ኢሕአፓ ህብረት አይፈልግም ወይም ከተባባረም እኔ የበላይ ልሁን፤ልቆጣጠር ብሎ ያስቸግራል ይባላል፡፡ ይህ ሀቅነት አለው?

መልስ-- ኢሕአፓ ለአንዳንድ ሰበብ ፈላጊዎች ወይም ድክመታቸውን ደባቂዎች አመቺ ነው የያሉት ይመስላል፡፡ የሕዝብ ደጋፍ ሲያጡ ኢሕአፓ ሻጠረን ይላሉ፡፡ ያቀዱት ሲባለሽ ኢሕአፓን ይከሳሉ፡፡ ድርጅቱ ደክሟል ይሉና በዚያው አፍ ደግሞ ትንፋሻችንነን ተቆጣጠረ ማለት ይቃጣቸዋል፡፡ የመለስም ቡድን ያው ነው፡፡ ኢሕአፓ አለ አንዴ ባለ አፉ ለችግሩ ሁሉ ኢሕአፓን በቀጥታና በእጅ አዙር እየከሰሰና እየወነጀለ አለ ፡፡ ህብረት አፈረሰ የሚሉትም የዚህ ዓይነት ናቸው፡፡ ራሳቸውን መመርምር ሲያቅታቸው ኢሕአፓን ይከሳሉ፡፡ ተቃዋሚ ሲነሳባቸወም የኢሕአፓ ሰርጎ ገብ ብለው ይመነጥራሉ፡፡ ይህ በተደጋጋሚ የታየ ነው፡፡
ኢሕአፓ ላይ የሚሰነዘረው ክስ መሰረተ ቢስ ለመሆኑ ተጨባጩ ሀቅ ምስክር ነው፡፡ ድርጅቱ ከተመሰረት ጊዜ ጀምሮ ከሌሎች መሰል ኃይሎች/ ጋር በመለስተኛ ፕሮግራም ዙሪያ  ለመተባባር ጥሯል፡፡ በአፀወ ኃይለስላሴ ጊዜ ኢብነአግ ከሚባል ድርጅት ጋር ብዙ ሙከራ ነበር፡፡ ከአፋር አንቅስቃሴ ድርጅትም ጋር በየካቲት 66 ተሞክሮ ነበር፡፡ ድርግ ራሱ የህብረት ጥሪ ሲያወጣ ኢሕአፓ በደፈናው ዞር በል ሳይል ህብረት እንዲመሰረት ሁሉን ሃይሎች ያቀፈና ያላገለለ መሆን አለበት ወዘተ

ብሎ በዴሞክራሲያ ልሳኑ ምላሽን ሰጥቷል፡፡ እኔ ካለሁ ሌሎች ለምን አስፈልገው አላለም፡፡ ወያኔንም ለህብረት ጋብዞ ብዙም ሞክሮ ነበር--ግን ወያኔ መተባባር አልፈለገም፡፡ከወያኔ ጋር ውጊያዎችም ከተደረጉ በኋላም ቢሆን የህብረቱ ጥረት አክቆመም ነበር ግን ወያኔ የታክቲክ የስትራተጂ ወዘተ ግንባር እያለ ተደናብሮ መያዣ መጨበጫ ሰልጣፋ ሳይሆን ቀርቶ ያው ግጭቱ ቀጠለ ፡፡ ከኢደኅ ጋር በየጊዜው ህብረት ተደርጎ ውጤትም ተገኝቷል፡፡በቶሮንቶ ካናዳም ህብረት ለመመስረት ከመኢሶንና ሌሎች ድርጅቶችም ጋርም ኢሕአፓ ተሰብስቦ ጥረታቸው ለባዕድ ባደሩ ቅጥረኞችና መሁር ተብዬዎች ቢከሽፍም-ቢዘገይም ኢደኃቅ ማለትም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያው ኃይሎች ቅንጅት ተቋቁሞ ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡ ይህን ግንባር ከፍሎ የወጣ የደርግ ኮለኔል በድርጊቱ ብዙ ጉዳት ቢያስከትልም ቅንጅቱ አስከ ቅርብ ጊዜ ታግሏል፡፡ በዚህ ቀውንጅት ኢሕአፓ ድምፁ ኬሌሎች ድርጅቶች ጋር እኩል ነበር፡፡ ቅንጅቱ በራሱ ሂደት መቆምና በሌላ መተካት ነበረበት፡፡ ይህም ኢዴኃኅን ለመመስረት የተደረገውን ጥረት ይመለከታል፡፡ ይህም ጥረት ሲጀመር ኢሕአፓ በእኩለ ተቀክሎ ድምፅም የሚወሰነው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ነበር፡፡ ኢዴኃኅን ለመሰረተው ስብሰባ የቀረቡት ሰነዶች ኢሕአፓ የፃፋቸው አልነበሩም፡፡ ውሳኔውም ሁሉ በግልፅ በድምፅ ብልጫ የተወሰነ ነው፡፡የኢዴኃኅ አመራር በዋና መልኩ በሀገር ቤት ነው፡፡ ኢሕአፓ በህብረቱ ያሉት ወኪሎች አንደሌሎች ድርጅቶች ሁሉ ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ቀሪዎቹን 28ኦቹን ተቆጣጥረው የፈለጉትን ያሰሯቸዋል ማለት መቸም የደርጅት መሪዎችን መናቅና ያልሆነ ነገር ማውራት ይሆናል፡፡ ከህበረቱ የወጡት ወደ ኢሕአፓ ጣት የጠቆሙት ይህን ማድርጉ ለድርጊታቸው ሽፋን ይሰጥልናል ብለው እንጂ ህብረት አፍራሽ ሆነ ለወያኔ የጠቀመውን አርምጃቸውን ማቋየቂያ ወይም ማሳበቢያ ኢሕአፓ ሊሆን አይችልም፡፡ ድርጅት ነን ብለው ግን አንደ በሳል ድርጅት መታገል አቅቷቸው ወያኔ የሚያምሳቸው ቡድኖች በቅድሚያ ራሳቸውን ማረም ማሻሻልና ተመክሮ ካላቸው መማር እንጂ ኢሕአፓን መወንጀሉ አያዋጣቸውም፡፡ አንዳንዶች በፕሮግራማቸውና በእንቅስቃሴያቸው የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ከመጣር ይልቅ በተቋቋሙ ማግስት በኢሕአፓ ላይ መዝመትን ይመርጣሉ፡፡ ይህ ወያኔን ሊያስደስት ቢችልም ለእነሱ በተጨባጭ የሚሰጣቸው ትርፍ የለም፡፡ ኢሕአፓ ባይኖር ደጋፊና አባል በብዛት እናገኛለን ብለው የሚያስቡ ነበሩ፤አሉም፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፡፡ ኢሕአፓ በተጨባጭ ልዩ ቦታ ይኑረኝ ፤ ከሌሎች የተለየ የበለጠ ድምፀ ይገባኛል ወዘተ ብሎ አያውቅም፡፡ በመለስተኛ ፕሮግራም መሰረት ለመተባባር ፍላጎት የሚየሳየው ማንም አስገድዶት አይደለም፡፡ ጠላት ባልሆኑ ድርጅቶች ላይም ሰርጎ ገብ አይሰድም፡፡ ለነገሩ የብዙ ድርጅቶች ምስጢር እባካችሁ እዩኝ-እወቁኝ በሚልበት ቢዜ እንጂ ሙያተኛ አሰራር ምስጢር መጠበቅን አስፍኖ ባለበት ጊዜ ላይ አይደለንም፡፡ የኢሕአፓ አባላት በያሉበት ሁሉ ህብረትና ግንባርን ለማጠናከር ይሰራሉ-- ይህ ደግሞ የሚጠበቅባቸው ነው፡፡ ኢሕአፓ በስራው አለሁ ማለቱ፤ አሰፈላጊውን መዋቅርና የሰው ኃይልማቅረቡ እንደ ፀጋና በጎ ነገር መወሰድ አለበት እንጂ በሌላ መተርጎም የለበትም፡፡ ኢሕአፓ ነፃ ድርጅት መሆኑን መርሳት አያሻም፡፡ ህብረትን ካልፈለገ አልፈልግም ማለት ይችላል፡፡ በህብረት ሰለሚያምን ግን ከሌሎች ጋር ሆኖ በጋራ ለመታገል የበኩሉን አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡ ማንም እንደሚያውቀው ደግሞ የኢሕአፓ ትኩረት በትግሉ ላይ እንጂ የራሱን ጣዖቶች ፈጥሮ አምልኳቸው፤ ክቡር መሪያችን÷ዶክተር ፕሮፌሰር፤ ሊቀ መንበራችን በሉልኝ የሚል አይደለም፡፡ ኢሕአፓ የሕዝብ ድርጅት አንዱ መለያ ትሁትነትና ራስን ከፍ ከፍ አለማድረግ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ሀቁ ይነገር ከተባለ የህብረትን

**ክንድ አዳክመው ኢዴኃቅንም ኢዴኃጎንም ጎድተው ለወያኔ የጠቀሙት እነማን እንደሆኑ ህዝብ ያውቃል፡፡**

**ይቀጥላል.....**

የኢሕአፓን ማንነት ለመረዳት ከዚህ በታች ያሉትን አንብበው የራስዎን አስተያየት ይገንቡ።

1. ማን ያውራ ቁጥር አንድ :- ኢሕአፓና የኦሮሞ ሕዝብ ትግልን የሚዳስስ
2. ማን ያውራ ቁጥር ሁለት፡- ኢሕአፓና የርዕዮተ-ዓለምን ጥያቄ የሚዳስስ
3. ማን ያውራ ቁጥር ሦሥት፡- ኢሕአፓና አገር ወዳድነትን የሚዳስስ
4. ማን ያውራ ቁጥር አራት፡- ኢሕአፓና የዴሞክራሲ ጥያቄን የሚዳስስ
5. ማን ያውራ ቁጥር አምስት፡- ኢሕአፓና ሕዝባዊ ራዕዩን የሚዳስስ
6. ማን ያውራ ቁጥር ስድስት፡- ኢሕአፓና የፖለቲካ ጥያቄን የሚዳስስ
7. ማን ያውራ ቁጥር ሰባት፡- ኢሕአፓና የፕሮግራም ጥያቄን የሚዳስስ
8. ማን ያውራ ቁጥር ስምንት :- ኢሕአፓና የሴቶች ጥያቄን የሚዳስስ
9. ማን ያውራ ቁጥር ዘጠኝ፡- ኢሕአፓና የልዑዓዊት ኢትዮጵያ የሀገር ጥያቄ የሚዳስስ
10. ማን ያውራ ቁጥር አሥር፡- ኢሕአፓና የካቲት 66ቱን ሕዝባዊ ዓመጽ የሚዳስስ
11. ማን ያውራ ቁጥር አሥራ አንድ፡- ኢሕአፓና ሀቀኛ ታሪኩን አስመልክቶ የሚዳስስ
12. ማን ያውራ ቁጥር አሥራ ሁለት፡- ኢሕአፓና ቅራኔዎችን አያያዝ በተመለከተ የሚዳስስ

13. ማን ያውራ ቁጥር አሥራ ሦሥት፡-
    በኢሕአፓ ላይ ለሚቀርቡ የውሸት ክሦች ጥያቄና ምላሽ ክፍል አንድ
14. ማን ያውራ ቁጥር አሥራ አራት፡-
    በኢሕአፓ ላይ ለሚቀርቡ የውሸት ክሦች ጥያቄና ምላሽ ክፍል ሁለት
15. ማን ያውራ ቁጥር አሥራ አምስት፡-
    በኢሕአፓ ላይ ለሚቀርቡ የውሸት ክሦች ጥያቄና ምላሽ ክፍል ሦሥት

ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብና ስለ ኢሕአፓ ለማወቅ :-

የኢሕአፓ ጽ/ቤት ቴሊፎን ለምትሹ
Washington D.C. Phone : 202-291-4217